*Association BOURGEONS*
*27 Rue André Tessier*
*94120 Fontenay sous bois*
*France*
*E-mail :* bourgeons.nbout@wanadoo.fr
*Tel : **00 33 1 48 77 46 06***
http://www.bourgeons.org/



እንደ አውሮፓ ቀን አቆጣጠር ፣
መስከረም 8 – 2019 ዓ/ም

በበጎ ፈቃደኝነት ተነሳሺነት ፣ በፈረንሳይ ኗሪ በሆኑ ኢትዮጵያውያኖችና በፈረንሳይ ተወላጅ ጓደኞሞች መካከል በኢትዮጵያ ውስጥ በችግር ላይ ወድቀው ርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችና ት/ቤቶች ፣ ያለባቸውን ችግር አብረዋቸው ለመካፈል ፣ የፈረንሳይ 1901 ዓ/ም ሕግ በሚፈቅደው መሠረት በአውሮፓውያን ቀን አቆጣጠር በ ሐምሌ 18 - 1996 ዓ/ም « Association Bourgeons » ፣ ሲነበብ "ቡርዣ" ሲተረጎም ደግሞ " እንቡጥ" በሚለው ስም ማኅበሩ ተሰይሞ ተቋቋመ ። በዚህ ሕግ አንቀጽ 1901 ስር የሚተዳደሩ ማኅበሮች ምንም የመተዳደሪያ ገቢ የሌላቸው ወይም በንግድ ዓለም ተሰማርተው አትራፊ ያልሆኑ ግብረሰናይ ማኅበሮች ናቸው ።
ስለዚህ እንቡጥ ወይም Bourgeons በዚህ ሕግ ስር የሚተዳደር በመሆኑ ፣ በመዋቅሩ ደረጃ ፣ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ወይም (NGO / Non-Governmental Organization) ያልሆነ በመሆኑ ፣ ከሌላ የውጭ ድርጅት ምንም ዓይነት ገቢ የሌለው ሲሆን ፣ የገንዘብ መዋጮ ፣ የጉልበት ፣ የዕውቀት ና የነጻ አገልግሎት ፣ ከበጎ አድራጊ አባሎቹ በሚሰጠው ልገሳ የሚተዳደር ፣ በበጎ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ የወንድማማቾች ማኅበር ነው ።

## እንቡጥ ወይም በፈረንሳይኛ አጠራሩ (Bourgeons) ሲነበብ ቡርዥ በመባል የሚታወቀው ይኸ ማኅበር -

- ዓላማ ፣ ለማን ና ለምን ተመሠረተ :-

ከላይ እንደተገለጸው ፣ የእንቡጥ ማኅበር በመጀመሪያ ደረጃ የተቋቋመው ፣ የትምህርት መማሪያ ቁሳቁስ መሳሪያ በችግር ምክንያት መግዠ ላጡ ወጣት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ሲሆን ፣ ከዚያም አልፎ አቅም ከቻለ ለሚያስተምራቸው ት/ቤት የማስተማሪያ መሳሪያዎችን በአቅርቦት ደረጃ ለመርዳት ነው ። በእርግጥ በአገራችን ያለው የትምህርት መማሪያ እጥረት ወሰን በሌለው ሁኔታ በየቦታው ቢከሰትም ከአንድ ቦታ መጀመሩ ግዴታ በመሆኑ ፣ ማኅበሩ ያተኮረው አዲስ አበባ ሾላ አካባቢ በየካ ወረዳ በሚገኘው ዓድዋ በር በሚባለው የመጀመሪያ ደረጃ የሕዝብ ት/ቤት ሲሆን ፣ ካለው አካባቢ ከነበረው ችግር አንጻር ነው ። ይህ ት/ቤት እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ (መጀመሪያ ግን እስከ 6ኛ ክፍል ብቻ ነበር) የቀለም ትምህርት የሚሰጥ ሲሆን ፣ ወደ 480 ተማሪዎች ገደማ ከማስተናገዱም በላይ 18 መምሕራኖችንም አቅፎ የያዘ ነው ።

- ምሥረታው ና መዋቅሩ :-

በእርግጥ የእንቡጥ (Bourgeons) ማኅበር መሠረታዊ ጥንስሱ በሕግ ከመመስረቱ በፊት ከ 1994 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 1996 ዓ/ም ድረስ ረዳት ለሚያስፈልጋቸው የዓድዋ በር የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ፣ ባለ ትዳር በሆኑት በወ/ሮ ካሚይ ና በአቶ ደጀን ይርጉ በግለሰብ ደረጃ ሲረዱ ከቆዩ በኋላ የችግሩ ክፍተት ሠፊ በመሆኑ ፣ በተናጠል ችግሩን ለመፍታት አልተቻለም ።
ስለሆነም ፣ በአንድነት ሆኖ ማኅበር ማቋቋሙ ለችግሩ መፍትሄ ሊሰጠው ስለሚችል እዚህ ነጥብ ላይ ተተኮረ ።
የእንቡጥ ማኅበር ፣ በፈረንሳይ ኗሪ በሆኑት ኢትዮጵያውያኖችና በፈረንሳይ ተወላጅ ጓደኞቻችን መካከል በበጎ ፈቃደኝነት ለነዚህ ርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ነገ ለሚተኩን ወጣት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ያለባቸውን ችግር አብረናቸው ለመካፈል ፣ የፈረንሳይ 1901 ዓ/ም በሚፈቅደው ሕግ መሠረት በ ሐምሌ 18 - 1996 ዓ/ም « Association Bourgeons » በሚለው ስም ማኅበሩን አቋቋምን ። ይኸውም ***« አንድ እርምጃ ወደፊት ተጓዝን ማለት ነው ! »***


ባጭሩ ማኅበሩን ስንመሠርት ወደ 10 የምንሆን ጓደኞሞች ነበርን ፣ ከዚያ ቀስ በቀስ ቁጥራችን በዝቶ በአሁኑ ወቅት የቢሮ አባላት ከቴክኒክ አማካሪዎች ጋር 13 ስንሆን ወደ 80 የሚጠጉ ማኅበርተኞችም አሉን ።



የእንቡጥ ማህበር ጠንሳሾች በከፊል

በ1994 ዓ/ም የመጀመሪያ ግኑኝነት ከአድዋ በር ተማሪዎችና አስተማሪዎች ጋር በከፊል







ፎቶው እንደ እንደእኛ በእድሜ የደከመ ቢመስልም በወጣቶቻችን ተክሷል

- የገቢ ምንጫችን :-

ማኅበራችን አትራፊ ና መንግሥታዊ ድርጅት ባለመሆኑ ፣ የመጀመሪያው ገቢያችን ከእያንዳንዱ አባል የምናገኘው ዓመታዊ ድጎማ ሲሆን ፣ በየዓመቱ የቀበሌያችንን አዳራሽ በማስፈቀድ ፣ ድግሥ በመደገስ ፣ ፓሪስ የሚገኙ የኢትዮጵያ ምግብ ቤቶች በሚያደርጉልን የርዳታ ምግብ አቅርቦት ፣ አንዳንድ ግዜም ሁኔታው ሲፈቅድ በስዊዝ ና በዳላስ የሚገኙ ወገኖቻችንም በሚያደርጉልን የመተጋገዝ ርዳታ ፣ የእንቡጥ ምስል ያለበትን ቲ-ሸርት፣ የሎተሪ ቶንቦላ ፣ ቅርሳቅርስ ፣ ፖስት-ካርድ ፣ የኢትዮጵያ ቀን መቁጠሪያ የመሳሰሉትን በመሸጥ ፣ በሚገኘው መጠነኛ የገንዘብ ገቢ ፣ ለተማሪዎችና ለት/ቤቱ ዕርዳታችንን በማበርከት እጅ ለእጅ በመያያዝ ፣ ከምስረታው ግዜ ጀምሮ ካለማቋረጥ አብረናቸው እየተጓዝን እንገኛለን ።

- የርዳታ አሰጣጥ ደረጃ :-

፩ ለ **150** ተማሪዎች በዓመት አንድ ግዜ በት/ቤት መግቢያ ሰዓት (መሥከረም ሲጠባ) ፣ ሙሉ የትምህርት ትጥቃቸውን እናሟላለን ። የተማሪዎቹ ቁጥር 150 የደረሰው የችግረኛ ተምሪዎቹ ቁጥር ጥያቄ ከፍተኛ በመሆኑ ነው ። ይኸም ሁሉ ሆኖ አቅማችን አንሶ ልባችን እያዘነ ፣ የባሰባቸውን በመውሰድ ፣ እጃችን እስከሚረጥብ ድረስ እንዲጠብቁ በመመዝገብ በቆይታ ትተን ያለፍናቸው በአሁን ሰዓት **45** ተማሪዎች አሉ ። በ 1996 ዓ/ም ላይ የነዚህ ተማሪዎች ቁጥር 16 ነበር ከዚያ ቀስ በቀስ 23 ፣ ከዚያም 53 ፣ 75 ፣ በመጨረሻም **150** ድረስ እንደ አቅማችን ቁጥራቸውን ከፍ አድርገናል ። *« ለሊጋሾቻችን ክብር ምሥጋና ይግባቸውና» !!*

፪ ወላጅ አልባ ሆነው ወይም አሳዳጊዎቻቸው በከፍተኛ ችግር ላይ ለተጋለጡ ለ 33 ተማሪዎች ፣ መንገድ ላይ እንዲሁ ወድቀው እንዳይቀሩ ፣ የማራቶንን ያህል የሩጫ ግብግብ በማድረግ ፣ በየቦታው ግለሰቦችን ተማልደን በአሁን ሰዓት ለእያንዳንዳቸው ረዳት (Sponsor) አግኝተንላቸዋል ። ስለዚህ ፣ እነዚህ በጎ አድራጊዎች በየወሩ የተወሰነ ገንዘብ ቆርጠውላቸው ፣ በባንክ በኩል ካለፈ በኋላ ፣ በእንቡጥ ማኅበር ተወካይ አማካኝነት ፣ ከት/ቤቱ በየወሩ ገቢያቸውን ይቀበላሉ ። በአሁን ግዜ ፣ እነዚህ ተማሪዎች ፣ በልተው ጠጥተው የትምህርታቸውን ቁሳቁስ ግዥ ችለው ካለሃሳብ በትምህርት ገበታቸው ላይ ይገኛሉ ። ወዲሁም ከረዳቶቻቸው ጋር በየግዜው ከሚያደርጉት የደብዳቤ መለዋወጥ አልፈው የአገራችንን ባሕል ስጦታ ከምሥጋና ጋር ሲሉኩላቸው ማየት የሚሰጠን ደስታ ከተራራ በላይ ነው .. *« ትምህርት የሕይወት ብርሃን ጉዞ ለመሆኑ ፣ የእነዚህ ታዳጊ ወጣቶች በአካልና በዕውቀት ማደግ ተጨባጭነቱን አሳይቶናል !!»* በዚህ አጋጣሚ ፣ ለነዚህ አኩሪ ተማሪዎች ልመናችንን ሰምተው እንደ ወላጅ ቤተሰብ በመሆን እዚህ ደርጃ ላደ ላደረሷቸው በጎ አድራጊዎች *ልባዊ ምሥጋናችንን እናቀርባለን ።*

፫ ለአጠቃላይ የት/ቤቱ ተማሪዮች ፣ የስፖርት ትጥቅ መግዣ ፣ ለት/ቤቱ የሥራ ማካሄጃ ማሟያ የመሳሰሉትን ወዘተ ት/ቤቱ በሚጠይቀን ጥያቄ ተመርኩዘን እንደ ገቢ አቅማችን ባጀቱን እናሟላለን ።

፬ ይህ የ ፬ ኛው የርዳታ ደረጃ ደግሞ ከሌሎቹ ለየት ያለ ነው ። ይኸውም ት/ቤቱ አንዳንድ ግዜ የድረሱልን ጥያቄ መልስ በማያገኝበት ግዜ እንደምንም ተረባርበን የበጎ አድራጊዎች ኪስ ተፈትሾ እንደ ገቢያችን ተራ በማሲያዝ በቅደም ተከተል የተደረገው የርዳታ ዓይነት ነው ። ለምሳሌ በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል ፣ በመጀመሪያው የት/ቤቱ ግንባታ ወቅት ወጭ መካፈል ፣ የስልክ መስመር ፣ የኤሌትሪክ ደወል ፣ ቴሌቭዥን ፣ የተማሪዎች መገናኛ ራዲዮ (Mini-media) ፣ Library of Association-Bourgeons በመባል ለተሰየመው መጽሐፍት ቤት የመማሪያ ና የልብ ወለድ መጽሐፍት ፣ ለት/ቤቱ የወረቀት ማባዣ መሳሪያ ፣ የፎቶ ኮፒ መሳሪያ ፣ ቪዲዮ ፕሮጀክተር ፣ ኮንፒተር ፣ ወንበር ጠረጴዛ ወዘተ የመሳሰሉት ይገኙበታል ።

- የተማሪዎቹ የትምህርት ይዞታ :-

የእንቡጥ (Bourgeons) ማኅበር ከተመሠረተ ግዜ ጀምሮ የተከታተልናቸው ተማሪዎች ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ እስከ ዩኒቨርሲቲ የደረሱ ፣ በሙያ ትምህርት ደግሞ በስልጠና ተሰማርተው ፣ የአስተማሪነት ፣ የሰዓሊ ፣ የመኪና ሜካኒክ ፣ የፀጉር ፣ የጋራዥ ፣ የኮንፒተር ፣ የሂሳብ አያያዝ ፣ የባንክ ሥራ ፣ የፀሐፊነት ደረጃ የደረሱ ተማሪዎች አሉን ። ከሌላው ለይቶ ስም መጥቀሱ ተገቢ ባይሆንም ፣ በ1998 ዓ/ም ላይ ያገኘነው የተሸከርካሪ ወንበር ተጠቃሚ የሆነው ዘመኔው ይማኖ ከዓድዋ በር ት/ቤት ተነስቶ ከጓደኛው የከለቡ ኃላፊ ዘላለም እንድሪያስ ጋር ኮተቤ በሚገኘው የመምሕራን ማሰልጠኛ ማእከል ውስጥ ስልጥንና ወስዶ በአሁን ወቅት የሂሳብ አስተማሪ በመሆን እያገለገለ ይገኛል ። ቀሪ ዝርዝሩ ረጅም ስለሆነ ወዘተ ብንለው ይሻላል ። ለማንኛውም ፣ ሁሉም አኩሪዎቻችን ሆነዋል !!

በዚህ አስደሳች ውጤታቸው ፣ ሰጭና ተቀባይ ብቻ ሳይሆን የሚመሰገነው ፣ *እንደ እርሾ ሆኖ ይህንን የትምህርት መሠረት ላስጨበጣቸው የዓድዋ በር ት/ቤትም ልባዊ ምሥጋናችንን ሳናቀርብ አናልፍም ።*







የዓድዋ በር ት/ቤት በቀበሌ ይተዳደር እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን በአሁን ግዜ ግን  ወደ ህዝብ  ት/ቤት  ዞሯል ።  በባጀትም ሆነ በቀሪው መስክ ከሌሎች ት/ቤቶች ጋር በእኩልነት ለመጓዝ በመቻሉ ታላቅ ዜና ነው ።   መኅበሩም  የተማሪዎቹን ብዛት የጨመረውም  አንዱ ምክንያት ለዚህ ነው ።

- የወጣቶች መረዳጃ ክለብ :-


  አንጋፋ ተማሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች ተበታትነው እንዳይቀሩ የመረዳጃ ክበብ ፈጥረንላቸው ፣ በአሁን ወቅት በችግራቸው ግዜ በመገናኘት እርስ በርሳቸው በመረዳዳት ላይ ይገኛሉ ። ከራሳቸውም አልፈው ረዳት ለሚያስፈልጋቸው ፣ ለ 4 ሕጻን ተማሪዎች በራሳቸው አነሳሽነት ፣ የዓመት ሙሉ የትምህርት ትጥቃቸውን አሟልተውላቸው በኩራት ወደ ት/ቤት እንዲሄዱ አድርገዋል ። *እንግዲህ የእንቡጥን ፋና የመከተል ፍንጭ ስላሳዩን የልጅ ልጅ እንዳየን ያህል  ስለተሰማን በደስታ ኩራት ፣ ተሞልተናል ።* በዚሁ እንደሚቀጥሉም ጽኑ ምኞታችን ነው !!


ተረጂ ሕጻናትና የክለቡ አባላተ በከፊል




ተማሪዎቹ በት/ቤቱ ግርጊዳ ላይ የጻፉት ጽሑፍ እንዲህ ይላል ፣






- ገበያ :-

  የትምህርትን ዕቃ መጠቀሚያ ቁሳቁሶች ፣ ከእርሳስ ፣ ከስፖርት ትጥቅ ፣ የትምህርት ሰጭ መሳሪያዎች ፣  ጀምሮ ከላይ ባጭሩ የተጠቀሱት በሙሉ በአገራችን ስለሚገኙ ፣ የተመኑም ሁኔታ ስለሚታወቅ ገንዘቡ ተልኮ የግገርው ሂደት እዚያው በአገሩ ገበያ ይካሄዳል ። ለምሳሌ ያህል ከዚህ በፊት ተማሪዎቹ ሕጻን በነበሩበት ግዜ ፣ ት/ቤቱ ለደንብ ልብስ ወይም ለዩኒፎርም ልብስ ሰፊዎች ጨረታ አውጥቶ አሸናፊው ነበር ልብሱን የሚሰፉላቸው ። ይህም እዚያ ያለውን ሰራተኛ ከመጥቀሙም በላይ ተጠቃሚውም ጭነት በማይኖርበት መንገድ እዚያው በዚያው ሁሉም ተባብሮ ይገበያያል ። በአሁኑ ግዜ ደግሞ ራሳቸው ወይም ከአሳዳጊዎቻቸው ጋር የትምህርት ፍጆታቸውን እዚያው ይገዛሉ ። ባለፉት ግዜአቶች 13 ኮንፒተር በገዛንላቸው ወቅት ፣ መቀመጫና ጠረጴዛዎቹ በአካባቢው አናጺዎች ነበር የተሰሩት ። ስለዚህ ባጭሩ ፣ በተቻለን መጠን  ከውጭ አገር ከመላክ ተቆጥበን ገበያው እንደ አገሩ እዚያው እንዲካሄድ እናደርጋለን ። እስካሁን ተሽከርካሪ ወንበር (Wheel-chair) ብቻ ነው ከዚህ የላክነው ። በዚህ አጋጣሚ ፣ ከዚህ የመላኩ ጉዳይ ታላቅ የራስ ምታት እንደሆነ መናገር እንወዳለን ። በቀረጥ ደረጃ



ተማሪዎች በእንቡጥ ማኅበር መጽሐፍት ቤት

- ማጠቃለያ :-

ማኅበራችንን ስንጀምር ፣ በመጀመሪያ ደረጃ ለእነዚህ ወጣቶች « የማንበብ ፣ የመጻፍ ና የሂሳብ ማስላት መሠረተ  ትምህርት ዕድል ከሰጠናቸው ባጭሩ በጣታቸው ከመፈረም ይድናሉ ፣ ከአዲሱም ዓለም ጋር ራሳቸውን የማስተዋወቅና የመተዋወቅ ዕድልም ይኖራቸዋል ፣ እዚህ ደረጃ ላይ ከተደረሰ ደግሞ ፣ የብዙ ሰው የሕይወት ጎዳና ተለወጠ ማለት ነው ። ዋናው መሠረቱን መጣል ነውና ! የሚል ነበር ሃሳባችን ። ምክንያቱም በጅምራችን ወቅት ይህን ያህል ዓመት ቆይተን የተማሪዮቹም የዕውቀት ደረጃ አድጎ በዚህ ሁኔታ ሕይወታቸው ይቀየራል ብለን አላሰብንም ነበር ።
ከማኅበሩ ምስረታ ጀምሮ በአሁን ሰአት በተለያዩ የሙያ ነክ መስመር ላይ የተሰማሩ **262** ተማሪዮች ራሳቸውን ችለው በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ሙሉ ተሳታፊ ለመሆን በቅተዋል ። አኩሪ የተማረ ትውልድ ማፍራት ምንኛ ያስደስታል ። ስለሆነም ፣ በነዚህ ዓመታቶች ውስጥ የቀሰምናቸው ነገሮች ቢኖሩ ፣ አንድን ሰው በችግሩ ወቅት ማዳን መቻል ማለት ያ ሰው ደግሞ ሌላውን የሚያድን በመሆኑ ፣ « የተደረገለት ግለሰብ ብቻ ሳይሆን ደስተኛው ፣ ማድረግ የቻለውም ዕድለኛ መሆኑንም ጭምር ነው » ስለዚህ ለማጠቃለል ያህል ፣ እነዚህ የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች (ከአባባ ተስፋዬ ሳህሉ አነጋገር የተወሰደ) ፣ በትምህርታቸው በርትተው " በለጋ ዕድሜያቸው ያንን ሁሉ የችግር ቸነፈር ተጋፍጠው ያሳለፉ በመሆናቸው " እኛንም አበረታተው አብረን እንድንጓዝ የመንፈስ ብርታት ሰጥተውናል ። ወደፊት ለዚህ ዓላማ በዚህ ጎራ ለሚቀላቀሉንም በአዲስ ሃሳብ ላይ አብረን ለመስራት ሰፊ ዕድል ከፍተውልናል ።

- ምሥጋና :-

በነዚህ ዓማመታቶች ውስጥ ሰለቸን ደከመን ሳይሉ ግዜአቸውን ገንዘባቸውን ና ዕውቀታቸውን ላበረከቱት የቢሮ አባላት ፣ አጠቃላይ የማኅበሩ አባላት ፣ በፓሪስ የሚገኙ የኢትዮጵያ ምግብ ቤቶች ፣ ስዊዝ (ሎዛን) አሜሪካ (ዳላስ) ፣ እንግሊዝ (ለንደን) ኢትዮጵያ አገር ቤት ላሉት ወገኖች ፣ የዓድዋ በር ት/ቤት ፣ እንዲሁም በርቱ ላሉን ሁሉ  ለዚህ ቅዱስና ክቡር ለሆነ ዓላማ ላደረጉት አስተዋጽኦ ሁሉ በታዳጊ ተማሪዎቹ ስም ሆነን እኛ የእንቡጥ (Bourgeons) ማኅበርተኞች ፣ ወሰን የሌለው ልባዊ ምሥጋና እናቀርባለን !!






የቢሮ አባላት በከፊል

ጅምር ሥራችን ይቀጥላል .....



የእንቡጥ (Bourgeons) ማኅበር ከፈረንሳይ :-

ሊቀ መንበር



ደጀን ይርጉ